**Department of Accountability and Research**

Alexandria City Public Schools
1340 Braddock Place, 3rd Floor
Alexandria, Virginia 22314

Phone: 703-619-8032
accountability@acps.k12.va.us
www.acps.k12.va.us/accountability

ጁን 2026

ውድ ወላጅ/አሳዳጊ፦

ከሜይ 4 እስከ ጁን 5 ቀን 2026 ባለው ጊዜ ውስጥ፥ ከአንደኛ ደረጃ 3ኛ ክፍል እስከ ሁለተኛ ደረጃ 12ኛ ክፍል ያሉ አብዛኛዎቹ የአሌክሳንድሪያ ተማሪዎች **የቨርጂኒያ የመማር ደረጃዎች (SOL) ምዘናዎችን** ወስደዋል። የቨርጂኒያ ኤስኦኤል (SOL) ምዘናዎች የተዘጋጁት በቨርጂኒያ የትምህርት መምሪያ (VDOE) ሲሆን፥ ከ3ኛ እስከ 12ኛ ክፍል ባሉ የተወሰኑ የትምህርት አይነቶች ላይ መወሰዳቸው ግዴታ ነው። ይህ ደብዳቤ ስለ እያንዳንዱ ተማሪ የኤስኦኤል ምዘና ውጤቶች አጠቃላይ መረጃ ይሰጣል።

የተማሪዎ የግል የኤስኦኤል ውጤቶች አብሮ በተያያዘው የወላጅ ሪፖርት ላይ ተገልጠዋል። የተማሪዎች አፈጻጸም ከ0 እስከ 600 ባለው የነጥብ መለኪያ የሚመዘን ሲሆን፥ 400 ነጥብ በቨርጂኒያ የትምህርት መምሪያ (VDOE) የተወሰነውን የብቃት ማረጋገጫ መመዘኛ የሚያመለክት ሲሆን፣ 500 ነጥብ ደግሞ ከፍተኛ ብቃትን ያሳያል። የቨርጂኒያ የትምህርት መምሪያ ለወላጆች ተጨማሪ መረጃዎችን ግልጽ እና ለመረዳት በቀለለ መልኩ ለማቅረብ የሚያስችል አዲስ የኤስኦኤል የወላጅ ሪፖርት (SOL Parent Report) አዘጋጅቷል። የተማሪዎትን ውጤት እንዴት መተርጎም እንደሚችሉ የሚያሳዩ ተጨማሪ መረጃዎችን እና ግብዓቶችን ለማግኘት፣ የተጠያቂነት እና ምርምር መምሪያ (Department of Accountability and Research) ድረ-ገጽን መጎብኘት ይችላሉ https://www.acps.k12.va.us/departments/accountability-research።

የተማሪዎትን ውጤት በሚመለከቱበት ጊዜ፥ ደረጃቸውን የጠበቁ ምዘናዎችን (standardized assessments) ጨምሮ በማናቸውም ፈተናዎች ላይ የሚመዘገቡ የክህሎት ውጤቶች ፍጹም ያልሆኑ መለኪያዎች እና «የመደበኛ መለኪያ ስህተት» (standard error of measurement - SEM) የሚባለው ሊያጋጥም እንደሚችል ማስታወስ አስፈላጊ ነው። ስለ መደበኛ የመለኪያ ስህተት (SEM) የበለጠ ለማወቅ እባክዎን ይህንን ድረ-ገጽ ይጎብኙ: Standard Error of Measurement | Virginia Department of Education

እባክዎን ልጅዎ ማናቸውንም የኤስኦኤል ፈተናዎች በወረቀት እና እርሳስ በድጋሚ ፈተና ወስዶ ከሆነ፥ ውጤቱ ሲደርስ የተሻሻለ "የወላጅ ሪፖርት" በፖስታ እንደሚላክልዎ ያስታውሱ።

ስለ ልጅዎ የኤስኦኤል ወላጅ ሪፖርት ማናቸውም ጥያቄዎች ካሉዎት፥ እባክዎን የተጠያቂነት መምሪያን (Department of Accountability) በስልክ ቁጥር (703) 619-8032 ያግኙ። ከተማሪዎ የውጤት ጋር በተያያዘ የትምህርት አሰጣጥን በተመለከተ ጥያቄ ካለዎት ደግሞ እባክዎን የተማሪውን ትምህርት ቤት ያግኙ።

ከሰላምታ ጋር፣



ዶር. ክሊንተን ፔጅ፣ የተጠያቂነትና የምርምር ዋና ኃላፊ
Department of Accountability and Research